# Park Hill School District
## የተማሪ የስነምግባር ደንብ
## መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የተማሪ የስነምግባር ደንብ መስፈርቶች የእያንዳንዱ ተማሪ የመማር መብት የተጠበቀበትን አካባቢ ለመፍጠር በትምህርት ቦርድ (ቦርድ) የወጡ ናቸው። በተለየ መልኩ በቦርድ ፖሊሲ ውስጥ ከተገለጸው በስተቀር፣ እነዚህ መስፈርቶች በሁሉም የትምህርት ቤት ህንጻዎች፣ በትምህርት ቤት ቦታዎች ወይም ስለ ትምህርት ቤት ቦታዎች፣ በሁሉም የትምህርት ቤት ተግባራት ወይም የPark Hill ትምህርት ቤቶችን የሚመለከቱ እንቅስቃሴዎች፣ ወይም ተሽከርካሪ ተማሪዎችን ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ በማንኛውም ተሽከርካሪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። የወላጅ እና የተማሪ መመሪያ መጽሃፍ እና ሁሉም የቦርድ ፖሊሲዎች በPark Hill School District ድረ ገጽ ላይ ይገኛሉ፣ www.parkhill.k12.mo.us። በወላጅ እና በተማሪ መመሪያ መጽሃፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ደንቦች እንዲሁም የተማሪዎችን ትክክለኛ ስነምግባር በተመለከተ በቦርድ ፖሊሲዎች ላይ የተቀመጡት ደንቦች በሁሉም ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ተማሪዎች የትምህርት ቤት ደንቦችን እና/ወይም የቦርድ ፖሊሲን ጥሰት በቀጥታ ለአስተዳዳሪው እንዲያሳውቁ ይበረታታሉ።

ተማሪዎች በስነ ምግባር ደንብ ውስጥ ያሉትን ደንቦች ማክበር አለባቸው። እነዚህን ደንቦች የሚጥሱ ተማሪዎች የቅጣት እርምጃ የሚወሰድባቸው ሲሆን ይህም መታገድ ወይም መባረር እና/ወይም ወደ ህግ አስከባሪ አካላት መላክን ሊያካትት ይችላል። የሚከተለው ሁሉንም የተከለከሉ የተማሪ ስነ ምግባር ወይም ሊሆኑ የሚችሉ ውጤቶችን አያጠቃልልም።

1. የPark Hill School District የጦር መሳሪያ መያዝ፣ መጠቀም፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ መግዛት፣ ማስተላለፍ፣ ማዘዋወር ወይም ማግኘትን ይከለክላል። የጦር መሳሪያ ባላንጣን፣ ባለጋራን ወይም ተጎጂን ለማጥቃት ወይም ለመከላከል ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል እቃ፣ መሳሪያ፣ ወይም የሚተኮስ ነገር፤ ወይም ሌላ ሰውን ለማስፈራራት፣ ለመዛት ወይም አካላዊ ጥቃት ወይም ጉዳት ለማድረስ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም እቃ ወይም መሳሪያ ተብሎ ይገለጻል። የጦር መሳሪያ ባላንጣን፣ ባለጋራን ወይም ተጎጂን ለማጥቃት ወይም ለመከላከል ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ወይም ሌላ ሰው ላይ ማስፈራሪያ፣ ዛቻ ወይም አካላዊ ጥቃት ወይም ጉዳት ለማድረስ ጥቅም ላይ የሚውልበት መደበኛ የትምህርት ቁሳቁሶችን፣ የቤት እቃዎችን፣ መሳሪያዎችን ወይም ሌሎች ቁሳቁሶችን ሊያካትት ይችላል። ይህንን ፖሊሲ የሚጥስ ማንኛውም ተማሪ ከትምህርት ቤት የሚታገድ ወይም የሚባረር ይሆናል። በተለየ መልኩ በቦርድ ፖሊሲ ውስጥ ከተገለጸው በስተቀር፣ አንድ ተማሪ ከሚከተሉት የጦር መሳሪያዎች አንዱን ወደ ትምህርት ቤት ይዞ እንደመጣ ከታወቀ፣ ተማሪው ከአንድ አመት ላላነሰ ጊዜ ይታገዳል ወይም እንዲባረር ይመከራል፦ መሳሪያ፣ ካርታ፣ ስውር የጦር መሳሪያ፣ ፈንጂ፣ የመሳርያ ድምጽ ማመቅያ፣ ሽጉጥ፣ ቢላ፣ በጣት ወስጥ የሚደረግ ብረት፣ ጠመንጃ፣ የተኩስ መሳሪያ (ቀስት፣ በአንድ እጅ የሚተኮስ ቀስት፣ ጠመንጃ፣ የቀለም ጠመንጃ፣ ወንጭፍ ወይም ሌላ መሳሪያ ያልሆነ የጦር መሳሪያ)፣ ጠመንጃ፣ ሾትገን እና/ወይም ጩቤ። የጦር መሳሪያ እንደ ጦር መሳሪያ የሚታወቅ ማንኛውንም መጫወቻ፣ በጦር መሳሪያ የተመሰለ ነገር፣ መሳሪያ የሚመስል ወይም ሌላ እቃን ሊያካትት ይችላል።
2. Park Hill School District አልኮል ወይም አደንዛዥ እጽን ይዞ መገኘት፣ መጠቀም፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ መግዛት፣ ማስተላለፍ፣ ማዘዋወር ወይም ማግኘት ወይም በእነዚህ ተጽዕኖ ስር መሆንን ይከለክላል።
3. Park Hill School District ቬፖችን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን ትምባሆ ወይም ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክስ ማጨሻ መሳሪያ መያዝ፣ መጠቀም፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ መግዛት፣ ማስተላለፍ፣ ማዘዋወር ወይም ማግኘትን ይከለክላል።
4. Park Hill School District የAC ፖሊሲን በመጣስ የሚደረግ ማንኛውንም አይነት ትንኮሳ ይከለክላል። እንደ ትንኮሳ የሚቆጠሩ ባህሪያት ስድብ መሳደብን፣ ክብር የሚነኩ ነገሮችን መጠቀምን፣ የዘር ወይም ሌሎች ማዋረዶችን፣ ተገቢ ያልሆኑ ቀልዶችን፣ ምስሎች ወይ የኤሌክትሮኒክስ ምስሎችን፣ የጥቃት ድርጊቶችን ወይም የንብረት ውድመትን የሚያካትቱ ሲሆን በእነዚህ ብቻ ግን አይወሰኑም።
5. Park Hill School District የAC ፖሊሲን ወይም የACA ፖሊሲን የሚጥስ ማንኛውንም አይነት ጾታዊ ትንኮሳ ይከለክላል። እንደ ጾታዊ ትንኮሳ ሊቆጠሩ ከሚችሉት ባህሪያቶች የጾታዊ ግፊቶች እና ጥያቄዎችን፣ ስድብ መሳደብን፣ ማዋረድን፣ ቀልዶችን፣ የሰውነት ምልክቶችን ወይም የወሲብ ተፈጥሮ ወይም በጾታ ላይ የተመሰረቱ ንግግሮችን እና የወሲብ ተፈጥሮ አካላዊ ንክኪን ወይም መንካትን የሚያካትቱ ሲሆን በእነዚህ ብቻ ግን አይወሰኑም።
6. Park Hill School District የተማሪ ጥቃቶችን፣ ጥል፣ አዲስ ተማሪ ላይ ተንኮል መስራት፣ ጥቃት፣ የሳይበር ጥቃት፣ ትምህርት ቤትን ማስፈራራት ወይም ሰውን ወይም ንብረትን በቃል ወይም በድርጊት ማስፈራራት እና/ወይም ሌሎች የጥቃት ድርጊቶችን ይከለክላል።
7. አንድ ተማሪ የትምህርት ቤቱን ደንቦች ለማክበር በእምቢታ መጽናቱን ካሳየ፣ ተማሪው መታገድን እና/ወይም መባረርን ጨምሮ የቅጣት እርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል።
8. Park Hill School District የተማሪ አለባበስ እና አለባበስ በጥንቃቄ የተያዘ፣ ንጹህ እና ጥሩ ጣዕም ያለው እንዲሆን ይጠብቃል። አለባበስ እና መዋብ የትምህርት ከባቢውን የሚያፋልስ አይሆንም። በርዕሰ መምህሩ ግምት የተማሪው መልክ ወይም የአለባበስ ዘይቤ የትምህርት ሂደቱን የሚያፋልስ ወይም ለጤና እና ለደህንነት አስጊ ከሆነ ተማሪው ማስተካከያዎችን እንዲያደርግ ሊጠየቅ ይችላል።
9. ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መኪና እየነዱ መምጣት መብት ነው። ቸልተኛ የሆነ ወይም ግድየለሽ በመሆን በትምህርት ቤት ንብረት ላይ ማሽከርከር፣ ወይም ሌሎች የመኪና ማቆሚያ ህጎችን መጣስ፣ መኪና የማቆም መብቶችን መሻርን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን የቅጣት እርምጃ ሊያስከትል ይችላል። (ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ)

ይህ የተማሪን ስነምግባር የሚያስተዳድሩ የቅጣት ደንቦች ከፊል ዝርዝር እና ማብራሪያ ነው። ተማሪዎች ሁሉንም ደንቦች ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። የስነምግባር ደንቡን ወይም የወላጅ እና የተማሪ መመሪያ መጽሃፍን በሚገመግሙበት ጊዜ ማንኛውም ጥያቄዎች ካለዎት እባክዎን የትምህርት ቤትዎን ርዕሰ መምህር ያነጋግሩ።

**የተማሪ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ስምምነት፦** ከዚህ በታች በመፈረም፣ የዲስትሪክቱን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ፖሊሲ እና አሰራርን እንዲሁ ለማክበር ተስማምቻለሁ። እነዚህን ድንጋጌዎች መጣስ የዲስትሪክቱን ቴክኖሎጂ ከማግኘት መታገድ ወይም መሻር እና ከትምህርት ቤት መታገድ ወይም መባረርን ጨምሮ በዚህ ብቻ ግን ሳይወሰን የቅጣት እርምጃ እንዲወሰድብኝ ሊያደርግ እንደሚችል እረዳለሁ።

የዲስትሪክቱን የቴክኖሎጂ መርጃዎች አጠቃቀሜ ግላዊ እንዳልሆነ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶቼን እና ሁሉንም የዲስትሪክት ቴክኖሎጂ መርጃዎችን ሊቆጣጠር እንደሚችል እረዳለሁ። በግዛት እና በፌደራል ህግ መሰረት፣ የዲስትሪክቱ የቴክኖሎጂ መርጃዎች ሩቅ በሆኑ ቦታዎች ተደራሽ ቢሆንም እንኳን የዲስትሪክት የቴክኖሎጂ መርጃዎችን በመጠቀም እንዲሁም የወረዱ ማስረጃዎችን እና የተሰረዙ ፋይሎችን ጨምሮ በዲስትሪክቱ የቴክኖሎጂ መርጃዎች ላይ ያስቀመጥኩት መረጃ ሁሉ ዲስትሪክቱ እንዲያቋርጥ እስማማለሁ።

**የስነ ምግባር ደንቡን አንብቤ ተረድቻለሁ እና ከላይ በትምህርት ቤት መምሪያ መጽሃፍ እና በቦርድ ፖሊሲዎች ውስጥ እንደተጠቀሰው ሁሉንም የPARK HILL SCHOOL DISTRICT የቅጣት ደንቦችን መከተል የእኔ ሃላፊነት ነው። እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ፖሊሲዎችን የሚያካትተውን የወላጅ እና የተማሪ መመሪያ መጽሃፍ የመስመር ላይ ቅጂ ማግኘቴን አምናለሁ። የPARK HILL SCHOOL DISTRICT ደንቦችን የማንበብ፣ የማወቅ እና የማክበር ሃላፊነት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ።**

| **በአብይ ፊደል የተጻፈ ስም**<br>ነጭ – የትምህርት ቤት ቅጂ | **የፊርማ ስም**<br>ቢጫ – የተማሪ ቅጂ | **የክፍል ደረጃ** | **ቀን** |
|---|---|---|---|